# እውን ወያኔ  አባይ ወንዝ እንዲገደብ ይፈልጋል?
# ክፍል ሁለት

ከደበበ ኃይሉ

በመጀመርያው ምዕራፍ የታላቁን አባይ ወንዝ ግድብ ግንባታ አስመልክቶ የወያኔን ባህርያት ጨረፍ ጨረፍ አድርገን ተመልክተናል። አያይዘንም ወያኔ ገና ድሮ መውደቅ ሲገባው እድሜው እንዲራዘም ከረዱትን በርካታ ምክንያቶች ውስጥ ዋኖቹ ሊሆኑ ይችላሉ የተባሉትን አስሩን ላይ ላዩን ዳሰናል። በተጨማሪም ይህ በ $4.7bn (£2.8 bn) ወጪ የሚገነባው ግዙፉ 1800 ስኩዌር ኪሎ ሜትር (695 ስኩዌር ማይል) መሬት የሚሸፍነው የአባይ ወንዙን የህዳሴ ግድብን አስመልክቶ ሰዎች ከሚሰነዘሯቸው ሃሳቦች ውስጥ አራቱን ግምቶች (assessments) አይተናል። አምስተኛውን አሁን እንጨምራለን። በጥሞና አናንብብ።

## 1. ግምቶች

ቁመቱ 170 ሜትር (558 ጫማ) ይደርሳል ተብሎ የሚገመተው በአፍሪካ ውስጥ ትልቁ የውሃ ኃይል ግድብ (Hydro power dam) ግንባታ ከተጀመረ ቆይቷል። የዚህን ግድብ ግንባታ አስመልክቶ ወገኖች የተለያዩ ግምቶችን ይሠነዝራሉ።  እነዚህኑ ግምቶችና አስተያየቶች ከሌሎች ፖለቲካዊና ኤኮኖምያዊ አዛማጅ ጉዳዮች ጋር እያነጻጸርን ለመመልከት እንሞክራለን።

አንደኛው ግምት ይህ ቤንሻንጉል ክልል ሱዳን ድንበር አጠገብ የተሰራው ግድብ በአመዛኙ ሲታይ ጥቅሙ ለሱዳን በመሆኑ መሬት የመሸጥ ልምድ የተጠናወተው ወያኔ ግድቡንም ለሱዳን ሊሸጠውና ለአሳዳጊው ግብጽ ውለታ ሊከፍል፣ አረቦቹን በማስደሰት የሥልጣን ዘመኑን እንደምኞቱ "መቶ ዓመት" ሊያደርግ ይችላል የሚል ነው። ከእባብ እንቁላል የእርግብ ጫጩት አይጠበቅም የሚሉ ወገኖች ናቸው።

ሁለተኛው ወገን ደግሞ ገና ከጅምሩ ታላቋን ትግራይ እገነባለሁ ብሎ የታገለው የብተና መንፈስ ዛር ተሸካሚው ወያኔ ግድቡን ወደ ትግራይ ከልሎ ምናልባት የኋላ ኋላ ከኤርትራ ጋር ይደባለቃል ወይም ኦሮምያን ካተራመሰ በኋላ ለኦሕዲድ ትቶለት ከአማራ ጋር ይደባለቃል በሚል ስጋት ነው። "ወያኔ በተፈጥሮው ከስህተቱ ሊማር የማይፈልግ ጸረ- ኢትዮጵያ ድርጅት በመሆኑ ፈጽሞ ሊታመን አይችልም" የሚሉት ወገኖች እዚህኛው ምድብ ውስጥ ይካተታሉ።

ሶስተኛቹ ወገኖች የግድቡን ግንባታ ደጋፊዎች የሚሰነዝሩት አስተያየት ደግሞ "ወያኔ ከዚህ ቀደም የተሳሳተ ርዕዮትን ተከትሎ ሃገሪቱን በዘር ከፋፍሏል፣ የባህር በር አሳጥቶናል፣ ሕዝቡ በሃገሩ ተመችቶት እንዳይኖር የስደቱ ሰለባ አድርጎታል፣ የኑሮ ውድነቱና ሙስናው ነዋሪውን አስመርሯል። ምናልባት ወያኔ ይህ በኮሙኒስታዊ እምነት ተነሳስቶ የፈጸመው በደል ተሰምቶት፣ የሠራው ኃጢዓት አላስቆም፣ አላስቀምጥ ቢለው ራሱን ቀይሮ፣ ለመላው ሕዝብ ብልጽግና አስቦ፣ ዘረኝነቱን በዜዴ ሊያጠብ እየተጋ፣ ይህንም ትልቅ ግድብ ካሳ አድርጎ ሊያቀርብና ሕዝቡን ይቅርታ ሊጠይቅ ይሆናል" ይላሉ። ስለሆነም "እስቲ እንጠብቅ፣ ፋታ እንስጠው ይሠራ፣ ተሸከሞት እኮ አይሄድም፣ ወያኔ እኮ እንደ ባላባታዊው ሥርዓትም ሆነ እንደ ደርግ ነገ ይወድቃል፣ ግድቡ ግን ቋሚ ነው" - የሚሉ ናቸው። ትዕግስትንና በጎነትን የተላበሰ አስተሳሰብ ነው።

አራተኞቹ የግድቡን መገንባት ፈጽሞ የማይቃወሙት ወገኖች ኢትዮጵያውያን የክርስትናው ዕምነት ኃይማኖት ተከታዮች የሆኑ ናቸው። "ትምክህተኞቹ ግብጾች እርሱ እግዚአብሄር አምላክ መሆኑን ያውቁ ዘንድ አባይን እንደሚያደርቅ በቃሉ ተናግሯል (ትንቤተ ሕዝቅኤል 29፣ 1-6) ይህ ትንቢት እንዳይፈጸም ግብጽ በሥጋና አዕምሮ ኃይል በመመካት ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ለማጥፋት በቁጥር አንድ ለዘመናት ተሰልፋለች። ዛሬ ግን የማይደፈር የሚመስለው ሁሉ በእግዚአብሄር ኃይል ተደፍሮ  አምላክ ወያኔን ተጠቅሞ ቃሉን ይፈጽም ዘንድ አባይን ሊያደርቅ፣ ውሃውን ሊቀንስ ወይም ያሻውን ሊያደርግ ይችላል። በመሆኑም የግድቡ ግንባታ የእግዚአብሄር ሃሳብ ሊሆን ይችላል፣ መጨረሻውን ማየት አለብን፣ አንቃወም" - ይላሉ።  ይህ መንፈሳዊ እምነት ላይ የተመረኮዘ አስተሳሰብ ነው።

አምስተኛውና የግድቡ ግንባታ ተቃዋሚዎች ሃሳብ ደግሞ ለየት ይላል። "የግድቡን መሠራት በመርህ ደረጃ አንቃወምም። ከግድቡ ግንባታ በፊት ግን የሠብዓዊ መብት ጥሰቱ ይገደብ። ሕዝብ ያልተሳፈበተ ግንባታ

ብቻውን እርባና የለውም። ወያኔ ለራሱ ዝና፣ ለራሱ የፖለቲካ ፍጆታ የሚያደርገውን የታሪክ እሽቅድምድምን እንቃወማለን፣ ከግድቡ ይልቅ የባህር በራችንን ማስመለሱ በቀደመ ነበር፣ ወያኔ የፖለቲካ ምህዳሩን አስፍቶ ለሃቀኛ ተቃዋሚዎች በሩን ክፍት ማድረግ አለበት፣ ተጽዕኖ የሌለበት ምርጫ ይደረግ" - የመሳሰሉትን ፖለቲካዊ ሃሳቦች የሚሰነዝሩ ናቸው። ይህ መልካም የፖለቲካ ምክር ልቦና ከተላበሰ ወያኔን የሚያነቃ፣ ካለፈው ስህተቱ የሚመልስ የሠላማዊ ትግሉ ዘርፍ ነው።

## 2. ግብጽ ማነች?

ግብጽ የጥቁር አባይ መነሻ የሆነችው ኢትዮጵያ ደመኛ ጠላት ነች። "በታኝ ፖለቲካ" ተዘርቶ፣ ታርሞ፣ ተለቅሞ፣ ታሽጎ ወደ ኢትዮጵያ የሚላከው ከግብጽ ነው። ጀብሃ፣ ሻዕቢያና ልጆቹ ኦነግ፣ ኦብነግ፣ የተረገዙት የወለዱት እዚያው ግብጽ ውስጥ ነው። እነዚህ ድርጅቶች አሁንም የግብጽን ምኞት ለማሳካት ይራወጣሉ። ኢትዮጵያ በዘር ተሸንሽናለች፣ የባህር በር አጥታለች፣ ዝናዋና ታሪኳ ተንቋሽዋል፣ ስደቱ ፈር እስኪለቅ ድረስ ማፈርያ ሆኗል። ታድያ እንደምን ለስልጣን ያበቃችው ሕ.ወ.ሃ.ት አባይን ሊያደርቅባት ወይም የውሃውን መጠን ሊቀንስባት አሰበ? ግብጽ ይህን እንደትልቅ ድፍረት ነው የተመለከተችው። "ለወግ ማዕረግ አብቅቼ" - የሚለው ውለታዋ ያብከነክናታል። በመሆኑም ከግለሰብ አንስቶ እስከትላልቆቹ የመከላከያና የውጭ ጉዳይ ኃላፊዎች ግድቡን አስመልክቶ ታላቅ ማጉረምረም አሰምተዋል። በዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ ውስጥ ግድቡ ግንባታው ሳይቋረጥ ሰላሳ በመቶው ያህል ተገባዷል ይባላል።

በዚሁ የፍሪካ ቀንዱ ተለዋዋጭ የትርምስ የፖለቲካ ሂደት ውስጥ በትላልቅ ወንዞቿ የተነሳ የእግዚአብሄር የቃል ኪዳን ሃገር ኢትዮጵያ ዋናዋ ሰለባ ነች። ጠላቶቿዋ ፈጥነው ወዳጅ ሆነው ተባብረው እንደ ጅብ ይነክሷታል። ወዳጆችዋም ሲከዷት ከጠላቷ ጋር አብረው ይወጓታል። ይህ ሁሉ ግፍ ምንም ያልጎደለባትን፣ የውሃዋን ማማ፣ የዳቦ ቅርጫትዋን ኢትዮጵያ ተጠቂ ያደርጋል።

"የኛ ኮፕቲኮች ኢትዮጵያውያንን ለክርስትና አበቃናቸው - እየሩሳሌም ውስጥ ያለው የኢትዮጵያ ንብረት (ዴር ሡልጣን) ወይንም (የንጉሡ ገዳም) ሆነ ኢትዮጵያ ራሷ የኔ ነች" - የምትለዋ ትልቋ የኢትዮጵያ ደመኛ ጠላት ግብጽ - በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ዝንተዓለም ጣልቃ የምትገባው ኢትዮጵያ አባይን የመገደብ አቅም እንዳይኖራት ለማድረግ ነው። ሌላ ምንም ምክንያት የላትም። ግብጽ በኢትዮጵያ ውስጥ አለመረጋጋት ሲፈጠር አባይ ወንዝ እንደማይገደብ ታውቃለች። የፖለቲካ መረጋጋቱ ቢኖር ሕዝቡ ሃሳቡን ወደ ልማት እንደሚያዞር ታውቃለች። የልማት ድፍድፎች እንዳይጣሉ፣ አገር አቋራጭ መንገድ እንዳይነጠፍ፣ የባቡር ሃዲድ እንዳይዘረጋ፣ የኢንዱስትሪው አንቀሳቃሽ የኤሌክትሪክ ኃይል አመንጪ ወንዞች እንዳይገደቡ የግብጹ የውጭ ጉዳዩ - "ትርምስ ኢትዮጵያ መምርያ" – ሌት ተቀን ይሠራል። "ኢትዮጵያ ድህነት የተንሰራፋባት፣ እርዛትና ረሃቡ የማያቋርጡባ፣ ዋይታ እንጂ እልልታ የማይሰማባት፣ የበሽታ፣ የጦርነትና የሰቆቃ ሀገር ሆና እንድትቀጥል ያላሰለሰ ጥረት አደርጋለሁ" ብሎ ቃል ያልገባ የግብጽ ፖለቲከኛ ወደ ስልጣን ወንበሩ አይጠጋም።

ግብጽ እንግሊዝና አሜሪካ የሚያወድሱለት የኃይለሥላሴ መንግስት ወድቆም አረካችም። አምባገነኑ ደርግ በጦርነት እንዲዋኸቅ፣ ፈጽሞ ስለልማት እንዳያስብ ለሻዕቢያ፣ ሕወሀት፣ ኦነግና ኦብነግ መጠነ ሠፊ እርዳታ ዘረገፈች። በትግራይ ክርስትያን ኢትዮጵያውያኖች ላይ አድሮ ሥልጣኑን በተቀናጀው ወያኔ ላይ እምነት መጣል ባለመቻልዋም ከሻዕቢያ ጋር ደም አቃባችው። እነሆ ሻዕቢያም መርዘኛና ቂምን ያዘለ ፖለቲካን እንዲከተል በመተት አደንዝዛ ለኦብነግና ኦነግ ዳግም ቱፍታ ሆነች። በሌላ በኩልም የተቀሩት ኢትዮጵያውያኖችን ቀልብ ለመሳብ ወያኔን – "ሕዝባዊ" - በሚመስል ዘዴ ለመጣል የትጥቅ ትግል ለሚያደርጉ ተቃዋሚዎች አነስተኛ መሬት እንዲሰጥና እንቅስቃሴውን የኤርትራ መረጃና ደህንነት ክፍሉ እንዲቆጣጠረው በማድረግ ደባ ከሻዕቢያ ጋር ተስማማች። ግብጽ ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት የሚቆረቆሩትን ወይንም ሕዝባዊነት የሚያንጸባርቁትን እንደነ ኢሕአፓ፣ መኢአድ፣ አንድነት፣ ኢዴፓ ወይም ሰማያዊ የመሳሰሉትን አትረዳም።

## 3. እውን ወያኔ የአባይ ወንዝ እንዲገደብ ይፈልጋል?

ወያኔ የአባይ ወንዝ እንዲገደብ፣ ተገድቦው ለኢትዮጵያ ህዝብ ጥቅም መዋል መፈለጉንና አልመፈለጉን

ለማውቅ ያዳግታል። የወያኔ ባህርይ በቅጡ አይታወቅም። የሚፈልግ ከሆነ ለምን የፖለቲካ መሻሻል አያደርግም?፣ ከሕዝብ አይታረቅም?፣ ለምን አማሮችም ሆኑ አፋሮች ከየአካባቢያቸው ሲፈናቀሉና ሲንቋሸሹ ዝም ይላል?፣ ለምን አብዛኛው ኦሮምያን የሚቆጣጠረው ኦሕዲድ በስልጣን ሲባልግ፣ በሙስና ሀገር ሲያጠፋ፣ ዘረንነቱን ሲያስፋፋ ዝም ይላል?፣ ለምን እውነተኛ ምርጫ እንዲደረግ አይፈቅድም?፣ ለምን ሴት እህቶቻችን በየአረብ አገሩ ሲሰደዱ፣ ሲደፈሩ፣ ሲገደሉ ዝም ይላል?፣ ለምን የኑሮ ውድነቱን አይቆጣጠርም?፣ ለምን መሬት ይሸጣል?፣ ለምን በግፍ ያሰራቸውን ታጋዮችና ጋዜጠኞች የሕዝብ ልጆች አይፈታም?፣ ሌላም ብዙ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ።

"ወያኔ የአባይ ወንዝ እንዲገደብ አይፈልግም" - እንዳይባል ደግሞ ለምን ይህን ሁሉ ወጪ ሸፍኖ ግንባታውን ያከናውናል? ለምን ካሳዳጊው ግብጽ ጋር ይወዛገባል? እውን ግድቡን ለሱዳን ሊሸጥ ነው? ወይንስ ቀድሞ እንዳሰበው ወደ ትግራይ ሊከልል ይሆን?። ግብጽ ለይስሙላ ያህል ነው የምትቃወመው ወይንስ ከወያኔ ጋር ሌላ የምስጢር ስምምነት አላት? የፖለቲካው ትንተና ብቻውን የማያበጥራቸው ብዙ ያልተፈቱ እንቆቅልሾች ድንገት ብቅ ይላሉ። ይሁንና ግን ወያኔ ግድቡን ለሱዳን ይሸጠዋል ወይንም ወደ ትግራይን ገንጥሎ የራሱ ያደርገዋል የሚለው ግምት በፖለቲካ ግምት ትክክለኛ መስሎ ቢታይም እግዚአብሄርን ለኢትዮጵያ ከገባው ቃል ኪዳን ጋር ይጋጫል።  ሱዳን የኢትዮጵያን መሬት ለመውሰድ አትችልም፣ ከወሰደችም በግድ ትመልሳለች። የትግራይ ሕዝብም ታላቅ ክርስትያን ሕዝብ ነው። ዓላማው ከሌሎቹ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፈጽሞ አይለይም።

## 4. እግዚአብሄር የአባይ ወንዝ እንዲገደብ ይፈልጋል?

እግዚአብሄር ቃሉን ያጸናል። ቃሉን የሚሽር የለም። ቃሉን የሰው ልጅ በአዕምሮ ጥበብ ሊይውቅና ሊያጠና በማይችልበት ሁኔታ በራሱ ጊዜ ያጸናዋል። በመጨረሳው ዘመን አባይ እንደሚደርቅና የግብጾችን ትምክህት እንደሚያጠፋ እግዚአብሄር ተናግሯል። አባይን የሚያደርቅባቸው ድርቅን በማስፋፋት፣ አውሎነፋስና ትነት በመልቀቅ ወይንም ኢትዮጵያ ግድብ እንድትሰራ ግብጽ ውስጥ አለመረጋጋት መፍጠር፣ ወዘተ ለመሆኑ መጽሃፍ ቅዱስ አይነግረንም። የእግዚአብሄርን ሃሳብ ግን አመልካች ድርጊቶችን እያየን ወይንም መንፈስ እየመራን ልንናገር እንችላለን።

እግዚአብሄር መለኮታዊ አሠራሩ ምስጢራዊ ነው። ንድፈሃሳብ፣ ፊሊጥ፣ ቀመር ወይንም ትንታኔ ሊፈለግለት አይችልም። በወንድሞቹ የተጣለውን ዮሴፍ አንግሶ ለጣሉት ሕዝብ መድህን አደረገው። ፈርዖን አልገባው ሲለው ልቡን አደነድኖ፣ የሞት ጥላ በግብጽ ላይ አስፍኖ፣ እሥራኤሎችን በሃይል እንዲለቅ አድርጎ ሠራዊቱን ሳይቀር ቀይ ባህር ውስጥ ሲያስጥማቸው አስቀድሞ ግን ይህንኑ ባህር በተዓምር ለሁለት ከፍሎ እሥራኤሎችን አሻግሮ ወደ ተስፋይቱ ምድር ከንዓን መራቸው። ልቡ ያበጠው ግዙፉ ጎልያድ ትንሹ እረኛው ዳዊት በወነጨፋት ደቃቅ ጠጠር ተጋደመ። አንበሳ ጉድግጓድ የተጣለውን ዳነኤል በአምላክነቱ ከልሎ አዳነው። እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ሲጠብቅ የኖረውም ሕዝቡን እንደ ዳዊት አንበሳ እያደረገና ጠላቶቿን እስከነ ትምክህታቸው እያኮሰሰላት ነው።

ከየክስተቶቹ መረዳት እንደምንችለው እግዚአብሄር "እሾህን በእሾህ እንዲሉ" አባይን ሊገድብ ፈልጎ የወያኔን ዕድሜ ሊያረዝም የፈለገ ይመስላል። የወያኔን ዕድሜ ካራዘሙት ምክንያቶች ዋነኛ ሊሆኑ የሚችሉትን በመጀመርያው ጽሁፍ ተመልክተናል። ተከዜ በረሃ ላይ ተጠፍጥፎ የተሰራው "ኦሕዲድ" የጡት ሀውልት እየገነባ ሕዝቡን ለወሳኝ  ለሙብቱ እንዳይታገል ወጥሮ በመያዝ የውስጡን ትግል አዳፈነ። ኢሕዴን (ብአዴን) የአማራውን ዘር ለማጥፋት ሲባል ተመሠረተ። የኢትዮጵያን ውርደትና ልመና መመልከት የሚያስደስታቸው "ምዕራብያኖች"፣ ግብረገብነትንና ሥነ-ምግባርን ለመናድ መጠነ ሠፊ ገንዘብ ወያኔን ይቸሩታል። ሕዝቡ ከኑሮው ውድነትና ከሥራ እጦት የተነሳ ወደ ውጭ እየወጣ ለዘመዶች የሚልከው "የስደት ገንዘብ" ወያኔን ኪሱን አሳበጠው። ኢትዮጵያን የማይወዱት፣ ክብሯ የሚያስፈራቸውና እድገትዋ ረፍት የሚያሳጣቸው "አንዳንድ ኤርትራውያንና (ሻዕቢያውያን) ኦሮሞዎች (ኦነጋውያን)" ሕዝባዊ ትግሉን ተደባልቀው ሊያወላግዱ ሲሞክሩ ባላሰቡት መንገድ ወያኔን ይጠቅም ጀመር። የነዚሁ ኤርትራውያንና ኦሮሞዎች መጋለብያዎቹ "የዲያስፖራው የትሮጃን ፈረሶች" እንደ ኦሕዲድ ማስተዋላቸው ተነጥቆ ለጠላቶች መድረክ ያመቻቻሉ። በጭብጨባ የተቀበሉት "ግንቦት ሰባት" መጠነ ሠፊ የዲያስፖራውን ገንዘብ ተሸክሞ ኤርትራ ውስጥ ገብቶ በሙተቱ ተቀሰፎ ሰጥሞ ሲቀር ኃላም የግብጽ ድጋፍ እንዳለው ድንገት ሲጋለጥ በንዋይ ድጋፋቸውን ሲቸሩት

የቆዩትን የውጭው ነዋሪ ኢትዮጵያውያንን ተስፋ አሟጠጠ። ይህ ሁሉ የፖለቲካ ሴራ የወያኔን ዕድሜ ሲያረዝም ለሠላማዊው ትግል እንቅፋት በመሆን ይበልጥኑ የኢትዮጵያን አንድነትን ፈተና ውስጥ ጣለው።

አንዳንዶች ታድያ "እንዴት እግዚአብሄር ሕዝቡ እንዲራብና እንዲጎዳ እያደረገ የሕዝብ ጠላት የሆነውን ወያኔን ዕድሜውን ያራዝማል? ሲሉ ይጠይቃሉ። መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማይ 21፣1-8 ወይም 2 ሳሙኤል 24፣1 ላይ እንዳነበብነው እግዚአብሄር ሰይጣንንም ቢሆን ተጠቅሞ የእሥራኤል ሕዝብ ወደ ቀድሞ ሥርዓቱ እንዲመለስ ቀጥቶታል። "ሰይጣን በእስራኤል ላይ ተነሳ፣ እስራኤልምን ይቆጥር ዘንድ ዳዊትን አንቀሳቀሰው" እግዚአብሄር ኢትዮጵያንም እየተመለከተ ነው። የቀድሞ ሥርዓት በመጥፋቱም ማዘኑ አልቀረም። እግዚአብሄር የኢትዮጵያ ሕዝብ እምነት ዳግም ብርቱ ይሆን ዘንድ ትምህርት እንዲማር ይፈልጋል።

ዛሬ ቤተክርስትያን በፖለቲካው ሰዎች እየተናወጠች ነው። የጥንቱ እምነት ተጨናግፎ፣ የባዕዱ አምልኮ ተስፋፍቶ፣ ግብረሰዶማዊነት ጥላውን አጥልቶ፣ የሰይጣን አሰራር ድፍረት አግኝቶ እነሆ ሀገሪቱ በዲያቢሎስ ጠፍር እጅና እግሯ ተጠርንፏል። አማኙ ይህን አስወግዶ ዳግም ግብረገብነት ስትመለስ እግዚአብሄር ሕዝቡን የስልጣኑ ባሌቤት ያደርገዋል። ቀድሞ ኢትዮጵያ ቤተ-ክርስትያን፣ ቤተ-ህዝብና ቤተ-አምልኮ የተዋሃዱባት ክርስትያናዊ መንግስት የቆመባት ሀገር ነበረች። እግዚአብሄር እየጨከነም ቢሆን ይህን ይመልሰዋል። እግዚአብሄር የኢትዮጵያዊው ነፍስ ሲያል ተከርችማ በድኑ አካል ጮማ እንዲቆርጥና ጠጅ እንዲያንቆረቁር አይፈልግም። ክርስትናና እስልምና ጎን ለጎን ሆኖና ተከባብሮ የሚኖረው ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ነው። ይህም የእግዚአብሄር ታላቅ ክብር መገለጫ ኢትዮጵያ በመሆኗ ነው። እግዚአብሄር አልመለስ ያሉትን እሥራኤላውያን ብዙ ጊዜ ሲቀጣ ቆይቷል። ይህ ለሕዝባችን ትምህርት ነው።

## 5. ምን እንማራለን?

በንጉሡ ዘመን በተማሪዎች ረብሻ ሰሞን በጀብሃ/ሻዕቢያ ኤርትራውያን አዋላጅነት ነፍስ ዘርተው እስከዛሬ ሲብላሉ፣ ሲያባሉ የከረሙ የልሂቃኑን የተበላሹ የፖለቲካ ውጥንቅጦች በወያኔው ዘመን ገሃድ እንዲወጡ ሆኗል። የብሄር ጭቆና፣ የአማራ የበላይነት፣ የሚኒልክ መስፋፋት፣ የመቶ ዓመት ታሪክ፣ የትግራይ መወረር፣ የኤርትራ ቅኝ ተገዢነት፣ ወዘተ እየተባለ በሻዕቢያ፣ ወያኔና ኦነግ ልሂቃን የሚለፈፉትን ባዶ የትርምስና የግጭት በታኝ እብለቶችን ሕዝቡ እንዲመረምር ጊዜ አግኝቷል። የኤርትራ መገንጠል ትርፍ የሌለው ኪሳራ ፖለቲካ መሆኑ በግብር ታይቷል። ሕዝብ መሃከል ተቀምጠው ከአብዛኛው የተሻለ እየኖሩ ተገንጣዮችን ሲረዱ የነበሩትን የሻዕቢያ ስውር አባሎችና አገልጋዮች በገዛ ዘመዶቻቸው ሲባረሩ የዋኹና ደጉም አብሮ መጨመሩ ፖለቲካ ምን ያህል ጨካኝ መሆኗን አሳይቷል። ወያኔ ኦነጎችን "ተገንጠሉ ፈረሱም ያው ሜዳውም ያው" ሲል እነ ጃዋርን "አንገነጠልም - አቢሲንያ ከሃገራችን ትውጣ" ወደሚለው ቧልት አውርዷቸዋል።

ከፋት ከፋትን ይወልዳል። ትላንት ወያኔ ሥልጣኑን ከደርግ ለመንጠቅ ሃሰትን ጠፍጥፎ "የብሄር ጭቆና"፣ "የአማራ የበላይነት"፣ "የሚኒልክ ወረራ" እያለ የትግራይ ልጆችን አሳሳቶ ተጠቀመባቸው። ኦነግም ሥልጣኑን ከወያኔ ለመንጠቅ ሲል ወያኔ ራሱ የለፈፈውን "የደደቢት የማደናገርያ ታሪክ" እንደ እውነት ቆጥሮ ከደቂቅ እስከ ልሂቅ ያሉ በርካታ የኦሮምያ ልጆችን በስሜት ሲነዳ ቆይቷል። ዛሬ "ፊንፊኔ ዙርያ ያሉት የኦሮምያ ልዩ ዞኖች በማስተር ፕላኑ እንዳይካተቱ"፣ "የነፍጠኞች ምልክት የሚኒልክ ሃውልት ይፍረስ"፣ "አፋን ኦሮሞ ፌዴራላዊ ቋንቋ ይሁን"፣ "ባህርዳር ላይ አማሮች ኦሮሞችን ሰድበዋል" - እየተባለ የሚናፈሱት "የትርምስ ቋንቋዎች" የመገንጠሉ ሃሳብ ማራገብያ የከፋት ሃሳቦች ናቸው። በከፋት የሚመጣ ስልጣን ደግሞ እንጦርጦስ የመውደቅን ያህል መውጫ ቀዳዳ የለውም። ለመላው ሕዝብ ነጻነትና ለሰብዓዊ መብት መከበር ታግሎ አምባገነንነትን በጋራ መጣል ሲገባ "የትርምስ የሃሰት ፖለቲካ ስልቶችን" ማስተጋባት ግብጽን፣ ሻዕቢያን፣ ኦነግን ወይም ኦብነግን ካልሆነ በቀር ለኢትዮጵያና ሕዝቦቿ አንዳች አይፈይድም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘርና ክልል ሳይለየው ይህንን ዓምደ ኢትዮጵያን መከፋፈያ የኑፋቄ ሤራ በአጽንዖት መታገል ይኖርበታል። ይህ የወቅቱ ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ ሊሆን ይገባል።

አንድ እውነታ አለ። ድክመትም ሊሆን ይችላል። ኢትዮጵያውያን ጀግንነት፣ ተባብሮ ሀገርን የወራሪ ጥቃትን የመመከት ኃይል እንጂ የዘመኑን የፖለቲካ ሽር ፈሊጥን በቅጡ አያውቁም። ከቅኝ ገዢዎቻቸው ይህንኑ ሻጥር የተለማመዱት ጀብሃውያንና ሻዕቢያውያን የመሬት ላራሹን ጥያቄ አወላግደው፣ በብሄረሰቦች መብት ለውሰው፣ ለኤርትራ መገንጠል ሲያውሉት በወቅቱ የነቁት ጥቂቶች ሲሆኑ ሰሚ ግን ሳያገኙ ቀሩ። ግብጽ

የሕዝባችንን ስነልቦናዊ አመለከከት በማጥናት ቋንቋችንን በሚናገሩት ተገንጣይ ስብስቦች እየተጠቀመች ሀገራዊ ሚስጢሮች እንዲሸፈኑብን በማድረግ ዓላማዋን ታሳካለች። የጠላት ሃሳብ ስውር ደጋፊዎች ዛሬም ከአንድ ማዕድ አብረውን በመቁረስ፣ ባንድ ዕድርና ማህበር በመመዝገብ፣ በየጉባኤው በመገኘት በፖለቲካ ያወዛግቡናል። በርካታ ኢትዮጵያውያን የግለሰቡ ጠባይ ሽጋ መሆኑን፣ ለተቸገረ ደራሽነቱን እንዲሁም ተግባቢ በለቅሶውና ሃዘኑ ፈጥኖ ደራሽነቱን እንጂ የተጠጋቸውን ግለሰብ ውስጣዊ ሸር ይመረምሩ ዘንድ ጊዜም እውቀቱም የላቸውም። መከራው፣ ረሃቡ፣ ድርቁ፣ ስደቱ፣ ድህነቱ፣ ጦርነቱና ሌሎችም ተከታታይ አበሳዎች የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመሰሪዎች ድብቅ ስልት አጋለጦ ሰጠው። ዛሬ ግን ከሞላ ጎደል ብዙዎች - ሻጥሮችን፣ ድብቅ ዓላማዎችን፣ የጠላትን አካሄድ እየተረዱ ሄደዋል። ሕዝቡ ቀስ በቀስ ከየዋህነት ወደ ተጠራጣሪነት፣ ከተጠራጣሪነት ወደ ጠንቃቃነት ተሸጋገረ። ፖለቲካ በጎ ሃሳቦችን ማጥፋቱ አልቀረም። ፖለቲካው ጎረቤት ወዳድነታችንንም ሆነ እንግዳ ተቀባይነታችን ላይ ተጸዕኖ ማሳረፉም አልቀረ። ምን ይደረግ።

ያም ሆነ ይህ በርካታ ሕዝባዊ ሃሳቦች እንዲንጸባረቁ ምሁራን በቅጡ በመጻፋቸው ለፖለቲካው ባህል መዳበር የሚሆኑ ትምህርቶችና ማብራርያዎች በተቻለ መጠን ተለቀዋል። በመሆኑም ሕዝቡ ከለይ የጠቀስናቸውን የፖለቲካ ትርምሶች ምንነት ሊመረምር ቢችልም ገና በቂ አይደለም። አሁንም በርካታ በጎ ታሪክንና ሳይንስን ያገናዘቡ ጽሁፎች ተለቀው ሕዝቡ ክፉና ደጉን እንዲያብላላ ማድረግ አለባቸው።

ለምሳሌ ኢትዮጵያን አንድ እንዲያደርጉና ቅኝ ገዥዎችን ለመመከት የእግዚአብሄር ኃይል የታጠቁትን ሚኒልክ ለማጥላላት ኦሕዲድ "ሀርካ ሙራ - ሐርማ ሙራ" (እጅ መቁረጥ - ጡት መቁረጥ) እያለ የሚነዛውን አመሰቃቃይ ሲያል-ወለድ የደደቢት መርዘኛ ቃላት የኦሮሞን ሕዝብ ከፋፍሎ ለኦነግ አጋልጦ እንዳይሰጥ ግንዛቤ ማዳበር ያስፈልጋል። በሰሞኑ የአምቦ ውዝግብም "ወያኔ" ለፖለቲካው ፍጆታ "ኦነግ" ደግሞ ለግንጠላው ፕሮፖጋንዳ እንዳያውሉት ሕዝባዊ ብስለት መጠቀም ያሻል። "አንድነት ኃይል ነው"፣ "የኦሮሞውም፣ ጋምቤላውም፣ አማራውም፣ አፋሩም ችግር የሁላችንም ችግር ነው"፣ "አንከፋፈልም" - ብሎ በህብረት መቆም አስፈላጊ ነው። የፖለቲካ ምህዳሩ ባልሰፋበት ሠላማዊ ተቃዋሚዎቹ ባገኟት ሜዳ የወያኔን ጫና ተቋቁመው ሕዝባዊነታቸውን ማንጸባረቅ ቢችሉም ፈተናቸው ቀላል አይደለም። የወያኔ ዱላ ፈጥኖ የሚያርፈው እነሱ ላይ ነው። በእርግጥ ትክክለኛ ታሪኩንም የማስተማር ሃላፊነት ሲጨምሩበት የደደቢቱ የከፋት ጉባዔ ሤራ እርቃኑን ይቀራል። ይህ ሁሉ መስዋዕትነት ነው የሕዝባዊ መንግሥቱ መሠረት።

የኋላ ኋላ ትግሉ ሲፈረጥም የሀገሪቱ አንድነትነት ጠላቶች (ቅኝ ገዥዎች፣ ግብጽ፣ ሻዕቢያ፣ ኦነግ፣ ኦብነግ) እንዲሁም ውላጆቻቸው (ስደት፣ ዘረኝነት፣ ጠላትን በጉያ የማቀፍ የዋህነት፣ የምዕራቡ ቅኝ ገዥዎች ያልተባረከ እርዳታና ነዋይ፣ ክፍፍል፤ እጠላት ጉያ ሥር ሄዶ የመወሸቅ የድንግዝግዝ መንፈስ፣ወዘተ) ይቀራሉ። ወያኔ ወደ እግዚአብሄር ሃሳብ ከተመለሰ፣ ለእውነተኛ ሕዝባዊ ምርጫ ከተዘጋጀ፣ ቂም በቀል ቆሞ በታሪክ ውለታው ይነሳል። የሰላማዊው ትግል ተለዕኮ ይህ ነው። እነሆ ጠላቶች አፍረው ኢትዮጵያ የአምላክ ክብር ማረፍያ ሆና ዳግም በሕልውናዋ ትቆማለች። የኢትዮጵያ ጎረቤት ሀገሮችም ፈሶ ከማያልቀው የኢትዮጵያ የበረከት ውሃና ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ እንደባረከው ዓይነት መጠነ ብዛቱ ፈጽሞ ከማይቀንሰው ዳቦ ይቋደሳሉ። ኢትዮጵያ የባህር በሯ ይመለሳል። የመገንጠል ምኞት ሞኝነት መሆኑም ይረጋገጣል።

## 6. ድምዳሜ

አንደኛ – ኢትዮጵያ፣ ለዜጎቿ በምትመች መንገድ፣ የእያንዳንዱ ባህል፣ ቋንቋ፣ ስነ-ልቦናዊ አመለካከት፣ ልማድና ታሪክ እንደተከበረ ሆኖ በኅልውናዋ እንድትቀጥል የምንመኝ ሁሉ እንዳለፉት አባቶቻችን ማስተዋል የተላበስን መሆናችንን ሳንተው የዘመኑን የጠላትን ስውር የዘር ክፍፍል ሴራና የፖለቲካ አካሄድ ማጤን ይኖርብናል። ፖለቲካችን ጥበብን ይጠይቃል። ስለሆነም በፖለቲካው መስክ ሁላችንም አውቂዎች ሆነን ለመታየት ከመፈለግ ይልቅ መላውንና ብልሃቱን ጸጋው ለተሰጣቸው ጥቂት ደጋጎች መተው ይገባናል።

ዛሬ ሃገራችን በርካታ ተዋናዮችን አፍርታለች። የድሮዎቹ በጣት የሚቆጠሩ ነበሩ። ገቢያቸውም ከዕጅ ወደ አፍ ነበረች። ዛሬ ድራማው፣ ቴአትሩ፣ ፊልሙ ይበልጥ አድጓል። በሙያው የተሰማሩት ኑሯቸውን አሻሽለዋል፣ ወደ ውጭ ይመላለሳሉ፣ ይሸለማሉ፣ ታዋቂ ሆነዋል። ድራማውና ፊልሙ ቆንጆ ቤት፣ ዘመናዊ አውቶሞቢልና ያማረ አውራ ጎዳና ያሳየናል። ከተራራው ኋላ ነባራዊው ሃቅ ግን ሌላ ነው። የተማረው ድንጋይ ፈላጭ ሆኗል። ውሃ ልትቀዳ እንሥራ ተሸክማ የሄደችው እናት ባዶ እንሥራ ተሸክማ ትመለሳለች። የኑሮው

ውድነቱ ደሃውን ተጭኗል፣ መብራት የለም። ጎዳና የተኙትን ጅብ እየበላቸው ነው። ትግል ተውኔት አይደለም። ትግል መሸለምያ፣ ወደ ውጭ መመላለሻና ኑሮን ማሻሻያ አይደለም። ትግል ከተራራው ኋላ የሚታየውን ሰቆቃ ማስቀርያ በማስተዋል የታጀበ መስዋዕትነት ነው። እነእስክንድር፣ ርዕዮት፣ አንዱዓለም፣ በቀለ ገርባ ሌሎችም ተዋንያን አይደሉም፣ አልተሸለሙም። ሽልማት ጸጋን ትቀብራለች። ገድላቸው ግን ነገ በተራዋ ከተራራው ኋላ ላሉት ታበራለች።

ሁለተኛ – ማስተዋሉን ከገዛ አዕምሯችን እያስነጠቅን በጠላቶቻችን ስውር ዓላማና የውሸት መንገድ ከተነዳን የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች "የታላቋ ኦሮምያ ቅዠት" ዕውን ሆኖ ዛሬ በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ የተጀመረው የአዲስ አበባን ማስተር ፕላን ህግ ቅዋሜ ነገም እንደ ትላንቱ ግብጽ በምትደግፋቸው ዘረኖች ድጋፍ እየተቸረለት ኦሮምያን አመሰቃቅሎ፣ የታላቁን ጀግና ኢትዮጵያዊ ኦሮሞን ሕዝብ ከኤርትራውያን ወገኖች በባሰ መከራ፣ ለስደትና ለከፋ አበሳ መዳረግ እንዳይመጣ ከወዲሁ ማሰብ፣ መምከር ያስፈልጋል። አንድነት፣ ሰላምና ብልጽግና - ክፍፍል፣ ሁከትና ምስቅልቅል የመሆኑን ነባራዊ ሃቅ በጎጂችን፣ በቤታችን፣ በእርሻና በሥራ ቦታዎች እንዲሆም በትምህርት ቤቶች ስንሆን በድፍረት መወያየት አለብን። ዓምደ ኢትዮጵያን ለማመሰቃቀል መሞከሩ የእግዚአብሄር እውነት ስትፈርድ ዋጋ መክፈልን ያመጣል።

እነሆ በመጀመርያው ገጽ ላይ የህዳሴውን ግድብ አስመልክቶ ከላይ ያየናቸው ሁለቱ አሉታዊ ግምቶች (negative assessements) አንድ ኢትዮጵያዊ በወያኔ ተፈጥሮ ላይ ካለው ጥርጣሬ አንጻር (skepticism) ወይም አንድ ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነ ግለሰብ ከከፋት የፖለቲካ ዘመቻ አንጻር (negative political campaign) ድብቅ ዓላማውን ማንጸባረቅያ ሊያደርገው ይችላል። ሶስቱ አዎንታዊ ግምቶች (positive assessements) ግን ከኢትዮጵያውያንና ከወዳጆችዋ  የሚሰነዘሩ ሲሆኑ በእርግጥ በአምስተኛው ተቃውሞ ላይ ግን ጠላት ሰርጎ ገብቶ መንገድ ሊያስት መሞከሩ አይቀርም። ለምሳሌ ኦነግና ኦብነግ፣ በግብጽ ርዳታና ባሻዕቢያ ግፊት በሙብቶችና ሃይማኖቶች ጥያቄ ዙርያ ሊያንገብቡ ይችላሉ።

በእርግጥ እስካሁንም ቢሆን የወያኔን ዕድሜ ያራዘሙትም ወገኖች ትምህርት ሳይቀስሙ አልቀሩም። እነሱ እንዳሰቡት ሳይሆን የወያኔን ዕድሜ እግዚአብሄር ለግንዛቤ፣ የፖለቲካ ባህል ማዳበርያና ለትምህርት ማስፋፍያ እንዲሁም ሕዝቡ እየተበደለም ቢሆን ሌሎች ጊዜው ሲደርስ ለሚነገሩ በጎ ሚስጥሮች አዋለው። አምላክ ሕዝቡ ወደ ቀድሞ ሃይማኖት፣ ግብረገብና ሥርዓት እንዲመለስ ይፈልጋል። በሌላ በኩል ደግሞ በጀግንነትና ብስለት የሚንቀሳቀሱት የሰላማዊ ትግሉ የሃገሬ አርበኞች ወያኔን በመታገልና በማዳከም ሕዝቡን ለመንግሥትነት ወደሚያበቃው ጫፍ ሲያደርሱ ወያኔ ገደል አፋፉ ላይ አቁመውታል። ሙስናው ፈሪ ያደረጋቸው ባለስልጣኖች ልጆቻቸው ወደ "ዲያስፖራ" እያሸሹ ሲሆን እነሱም ሊከተሏቸው ያስባሉ። ባለማስተዋል፣ በችግር ወይም ቅንጦት የተነሳ "ዲያስፖራ" የሆነው ወገኔም በኩራት ወደ ሃገሩ ይመለሳል። ኢትዮጵያ እነግብጽና መሰሎቿ ከደገሱላት ምስቅልቅል እንድታመልጥ አስቀድሞ የተወጠነው የእግዚአብሄር ምስጢራዊ ሥራ ብዙ ነው። እግዚአብሄር ሲረዳን ወደፊት እንጽፈዋለን።

የአባይ ወንዝ ግንባታም ሆነ ፍጻሜ የአምላክ ሥራ ሊሆን ይችላል። በእርግጥ ለፍጻሜ ከበቃ ግብጽ ለዘመናት በሃገራችን ላይ የምትሸርበውን ሸር ለማቆም ትገደዳለች። ዋነኛው ችግር ተቀረፈ ማለት ነው። በግብጽ ድጎማና እርጥባን የሚተዳደሩትም ቅጥረኞች ቁርጣቸውን ያውቃሉ። በሌላ በኩል ደግሞ የጥቁር አባይ የኅዳሴው ግድብ ግንባታ የእግዚአብሄር ሃሳብ ቢሆንም እውስጡ በርካታ የፖለቲካ እንቆቅልሾችንና ውጥንቅጦችን ማዘሉ አይቀርም። ጭፍን ድጋፋችን አምባገነኑን ወያኔን ማወፈር - ጭፍን ተቃውሟችን ደግሞ ግብጽን፣ ሻዕቢያን፣ ኦነግን፣ ኦብነግንና ሌሎች ፀረ-ኢትዮጵያውያኖችን ማገዝ፣ የሀገሪቱን ሉዓላዊነት መናድና መለኮታዊ ህጎችን መጻረር እንዳይሆን - ግራና ቀኙን መቃኛ፣ ወደፊት አማትሮ ማያ መነፅር በአንገታችን ላይ በማንገት ጥንታዊው ማንነታችንን ማሰስና የአባቶቻችንን ፈለግ መከተል አለብን።

ጥላቻንና ችኩልነትን ያስወገደ፣ ማስተዋልና ብልህነትን እንድንላበስ - የማይተወን፣ እስከዛሬም ያልተወን አምላክ በቸርነቱ ይርዳን።

እግዚአብሄር ይመስገን

ጸሃፊውን በ debebehailu321@gmail.com ማግኘት ይቻላል